# “ማኅበረ ቅዱሳን”፡ አገር በታኝ ትውልድ ገዳይ የጽንፈኞች መናገሻ ነው!



ሌላው ይቅር እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ ጥርት ያለ ግብና ዓላማ የለውምና (አልነበረውምና) በኢትዮጵያ ውስጥ በፍጥነት ተነስቶ በተነሳበት ፍጥነት ያልከሰመ፣ እንደ ጥላ ታይቶ ላሽ ያላለ፣ ዝናብ እንደሌለው ደመና አንዣቦ ሲያበቃም ብን ብሎ ያልጠፋ የኢትዮጵያ ህዝብ ጉልበት ያልበላ ጊዜያዊ እንቅስቃሴ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሙብት ለመግፈፍና በአንጻሩ ደግሞ የአንድ ብሔር ፍጹም የሆነ የበላይነት ለማንገስ በሚደረገው መላላጥ ሁሉ ያልተሞከረ ወይም መጠቀሚያ ያልሆነ የማኅበረሰብ ክፍል (እንቅስቃሴ) የለም። አንዳቸውም ውጤት አላስመዘገቡም እንጅ ሁሉም ነገር ተመክሮዋል። በከፈተኛ ተቋማት የሚደረገው ትንኮሳና ግርግር፤ ጎሳን ያማከለ ሊነሳ የሚፈለገው ግጭትና ትርምስ፤ ኃይማኖታዊ ተቋሞች በሽፋንነት መጠቀምና ሌሎች በርካታ መንገዶች ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው።

እስልምና የራሱ አጀንዳ ይዞ ሲነሳ የእኛዎቹ (ሳይዘሩ ማጨድ ሳይቀቡ መንገስ የሚያምርባቸው ፖለቲከኞቻችን) ደግሞ ከየትም ከትም ተጠራርተው “ድምጻችን ይሰማ!” እንደ ጀልባ ሲንጠላጠሉበት ጀልባዋ ሰጠመች። የዋልድባ ጉዳይም እንደዚሁ “የስኳር ፋብሪካ በትግራይ ክልል መተከል የለበትም!” የሚለውን ስውር አጀንዳ “ቤተ ክርስቲያን ተደፈረች!” የሚል ሽፋን ተሰጥቶት ሲጮኽና እሳት ለማያያዝ ሲሞከር ይህም በሚገርም ሁኔታ ሳይሰምር ቀረ። አሁን ደግሞ “ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞተዋልና የሞተውን እባብ “ጸበል” ረጭተን ለምን ግርግር ፈጥረን ህልማችንን እውን አናደርግም (ምኒሊክ ቤተ መንግሥት አንገባም!)” በሚል ስሌት በነጻ ፕሬስና በጋዜጠኝነት ስም ነገር ፍለጋ “ማኅበረ ቅዱሳን ይቅደም!” የሚል መፎክር ተይዞ ዘመቻ ተጀምሯል።

ለመሆኑ “ማኅበረ ቅዱሳን” ማን ነው? በማንና እንዴትስ ተመሰረተ? ዓላማውና ግቡስ ምንድ ነው? መንፈሳዊ ካባ የተላበሰና በስም ያማረ በቤተ ክርስቲያን ሥር እንደ ማኅበር ለመደራጀትም ሆነ ራሱን ችሎ ለመቆም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት አለው? የዚህ መሰሪ ድርጅት ህቡእ የፖለቲካ ተልዕኮውስ ምን ይመስላል? ለሚሉና ሌሎች በርከት ያሉ “በማኅበረ ቅዱሳን” ዙሪያ ሊያነሱት የሚችሉት ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መልስ ያገኙ ዘንድ ቀጥሎ የተቀመጠውን ሊንክ ይጫኑ። [http://salsaywoyane.files.wordpress.com/2013/10/assocaition-of-saints-or-association-of-the-davil.pdf]

## ልዩ ማስታወሻ፥

መዋቹ ጠቅላይ ሚኒስትር በኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኘት በምድሪቱ ሥር እየሰደደ የመጣውን የኃይማኖት ጽንፈኝነት በማስመልከት ያደረጉትን ንግግር ተከትሎ እኔም መዋቹ ጠቅላይ ሚኒስትር በመደገፍ ሳይሆን እንደ አንድ ዜጋ ጽንፈኝነትንና ጠባሳውን፤ በተጨማሪም አንድ ራሱን “ክርስቲያን ነኝ!” ብሎ የሚጠራ አማኝ/ግለሰብ ሆነ ድርጅት ሌላ ድብቅ አጀንዳ ከሌለው በስተቀር ከጽንፈኝነት ጋር ምንም ዓይነት ክፍልም ሆነ ሕብረት እንደሌለው ጽንፈኝነት ጸረ ክርስትና እንቅስቃሴ ለመሆኑ ለማመላከት ከሥነ መለኮት ዕይታ “«አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት» የሚለው አባባል “ሕገ መንግሥት” ላይ ብቻ ሳይሆን በክርስትናም ላይ የተቃጣ የጸረ ክርስቶስ ሃሳዌ መሲህ አጀንዳ ነው!” በሚል ርዕስ እ.አ.አ ሚያዝያ 2012 ያዘጋጀሁት ጽሑፍ  ሆኖ በወቅቱ በዳያስፖራ አከባቢ የኢትዮጵያ ጉዳይ ከማንም በላይ ይመለከተናል ለሚሉ የድረ ገጽ ባለቤቶች ለንባብ ያበቁት ዘንድ ብልከውም አንዳቸውም የተላከላቸው ጽሑፍ ለንባብ ያበቁት ዘንድ አልደፈሩም።

ይህ ጽሑፍ “ቀጣዩ የኢህአዴግ ዒላማ ‘ማህበረ ቅዱሳን’ ይሆን?” በሚል ርዕስ በተመስገኝ ደሳለኝ የተጻፈው ጽሑፍ ላስነበቡን ድረ ገጾች በሙሉ ተልኳል።

## ሐተታ፥

የምዕራቡ ዓለም የዕድገትና የስልጣኔ ምስጢር በማውሳት ሐተታዬን ልጀምር። ለብዙዎቻችን ግልጽ እንደሆነ የምዕራቡ አለም ፖለቲካ ከተቀረው የዓለማችን ክፍል የሕዝብ አስተዳደር የተለየና የላቀ የሚያደርገው ቢኖር የፖለቲካ መሪዎች የሃሳብ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በሚደርሱት የጋራ ውሳኔ፣ አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት ለመሆኑ አያከራክርም። ለምሳሌ ያክል "የዲሞክራሲ" ተምሳሌት መሆንዋን በሰፊው የሚነገርላት ልዕለ ሃያልዋ ሀገረ አሜሪካ የወሰድን እንደሆነ በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በየትኛውም መስክ ያለ ተቃናቃኝ በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው መድረክ የበላይነትዋን እንደያዘች የመዝለቅዋ ምስጢር ስልጣን ላይ የሚወጡትም ሆነ በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፉትን የፖለቲካ መሪዎች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ውጤት ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም። ይህ ማለት ዲሞክራትም ይሁን የሪፐብሊካን ፓርቲ አቀንቃኝ ሀገራቸው አሜሪካ በዋናነት ልትከተለው በሚገባት ፖሊሲ ላይ የጎላ ልዩነት ቢኖራቸውም የአሜሪካን ሉዓላዊነት እንዲሁም የአሜሪካ ሕዝብ ጥቅም የመጣን እንደሆነ ግን አንዱን ከሌላውን መለየት ፈጽሞ አይቻለንም። ሀገራዊ ጥቅም በተመለከተ ዲሞክራቱም ሪፖብሊካኑም አሜሪካዊ ነው!! እናማ ከየትም አቅጣጫ ቢመጡ ይህ ጽሑፍ ሲያነቡ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ በሰከነ መንፈስና በተረጋጋ ልብ ያነቡት ዘንድ ስጠይቅ በአክብሮት ነው።

መዋቹ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በወቅቱ በኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ካደረግዋቸው ንግግሮችና ከሕዝብ ተወካዮቹም ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ካነሱዋቸው ነጥቦች መካከል ሃይማኖትን በማስመልከት መንግስታዊ ትንታኔአቸውና አቋማቸውን ለፓርላማው ግልጽ አድርገዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ማህበረ ቅዱሳን" ከአልቃይዳ ጋር በማመሳሰልም ገልጸውታል። እንግዲህ ይህን አገላለጽ/ንግግር ያዳመጠ ሰው አልቃይዳ ማለት ደግሞ ማን ነው? ምንስ ማለት ነው? ብሎ የሚጠይቅ አዋቂ ሊኖር እንደማይችል አምናለሁ።

አልቃይዳ በብዙሐን የንጹሐን ዜጎች ደም ተጠያቂ: በደም የተነከረ መታወቂያ ያለው: መሰረተ ልማቶችን በቦንብ የሚያጋይ: በአጠቃላይ በንጹሃን ሰዎች፣ በልማት ተቋማት፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ንብረቶች ላይ ያነጣጠረ የሽብር ጥቃቶች የሚፈጽም ጸረ ልማትና በግርግር የሚያምን ሃላፊነት የጎደለው ሃይል ነው በአንጻሩ ደግሞ "የቅዱሳን ማህበር" ሲል ራሱን በቁልምጫ ቋንቋ የሚጠራ:

- ለነውሩ መንፈሳዊ ካባ ያጠለቀና የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ፥
- ታቦት ተቀርጾለት አምልኮ ብቻ የቀረው፥
- በኢየሩሳሌም በሶሪያ ... የሚገኝን የተቀደሰ ተራራ ነው እያለ ተራራ እያሳለማ ሲዘርፍና የአማኞች ኪስ ሲያራቁት የኖረ፥
- ላለፉት ሃያ ዓመታት በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ስም ከእምነትዋ ተከታዮች አልፎ በሀገርና በትውልድ ጫንቃ ላይ እንደ መዥገር ተጣብቆና ተቀምጦ ይሄ ነው ተብሎ በቀላሉ የማይገመት የአገር ሀብትና ንብረት በሕገ ወጥ መንገድ ስያግበስብሰና የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ሲዘርፍ እዚህ የደረሰ፥
- በብዙዎች የቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ልጆች ደም የተጨማልቀ ነፍሰ ገዳይ፥

- ከቤተ-ክርስቲያን አልፈው ለሀገር የሚተርፍ እውቀት ያላቸውና በጥበብ የተሞሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለስደትና ለግዞት ህይወት የዳረገ፣ ሀገር ወልዳ እንዳልወለደች የወላድ መሃን ያደረገ፥
- የህልውናው ያክል ጸበኛ፣ አልታዘዝ ባይና አመጸኛ ትውልድ በማፍራት አቻ የማይገኝለት፥
- በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ታሪክ ምእመናን ከመሪዎች፣ አባቶች ከልጆች ጋር እንደ አንድ አካል መደማመጥ ይሳናቸው ዘንድ የአለመግባባት መንፈስ ያስተጋባ፥
- የተለያዩ ያማሩ ስሞች ያሏቸው ድረ ገጾች በመክፈት በቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ጭምር ሳይቀር ጦርነት የከፈተ፥
- ለምንም ለማንም በማይበጁ ያልተጠኑና ቤተ ክርስቲያን በሕግ የማታውቃቸው እንግዳ ትምህርት በማሰራጨት ሃይማኖትን የሚበርዝ፣ ትውልድን የሚያደነዝዝ ሰላቢ ነው።

በአጠቃላይ “ማኅበረ ቅዱሳን” ክርስቲያናዊ ድርጅት ሳይሆን ጸረ ክርስቶስ ወንጌል የተደራጀ አጽራረ ጽድቅ፤ መከፋፈልንና ሁከት እንደ አጀንዳ ቀርጾ ነውጥን በመፍጠር ምኞቱን የሚያሳካ ሀገር በቀል የጥፋት ተልእኮ ያነገተ ጽንንፈኛ የማይገልጸው አውዳሚ ነፍሰ ገዳይ ማኅበር ነው።

* * * * *

## እንደ “ማኅበረ ቅዱሳን” ያለ በኃይማኖት ሽፋን ህቡዕ የፖለቲካ አጀንዳ የሚያራምዱ ጽንፈኞች መዋጋት የዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው!

ራሱን “ማኅበረ ቅዱሳን” ሲል የሚጠራ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ጉያ ላይ ተወሽቆ በመንፈሳዊነት ስም ስለ ተቋቋመው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት የሌለው መሰሪ ድርጅት በማስመልከት መንግስት የሀገርና የሕዝብን ሰላም የመጠበቅ ግዴታው ነውና በመግቢያዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት መዋቹ ጠቅላይ ሚኒስትር በኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ፊት ቀርበው ባደረገሩት ንግግር ላይ የሰይጣን ማህበር “ማህበረ ቅዱሳን” ለመግለጽ የተጠቀሙበት አገላለጽ እርምጃው ሀገራችንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ማእከል ያደረገ እስከሆነ ድረስ እኔም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የተናጋሪው ሃሳብና አቋም ሙሉ በሙሉ በመጋራት አንኳር አንኳር ነጥቦችን በማተኮር እንደሚከተለው ሐተታዬን ይዤ ቀርቤአለሁ።

መዋቹ ጠቅላይ ሚኒስትር በተለያዩ ሃይማኖቶች የጽንፈኝነት ምልክቶች መታየታቸውን አውስተው በምሳሌነት ከጠቀሱት መካከል በአዲስ አበባ የተከበረውን የጥምቀት በዓልና  የማኅበረ ቅዱሳን ጸረ ሕገ መንግስታዊ እንቅስቃሴው የገለጹት በእንዲህ ዓይነት መልኩ ነበር “ጥምቀት ላይ ከነበሩ መፎክሮች አንዱ «አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት» የሚል  ነው።”

የማኅበሩ አፍራሽና ጸረ ሕገ መንግስታዊ ድርጊት ሲያስረዱም ምክንያታቸው እንደሚከተለው አቅርበዋል «አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት» የሚል ሕገ መንግስት የለንም። አንድ ሀገር የፈለገውን ዓይነት ቁጥር ያለው ሃይማኖት ነው ህገ መንግስቱ የሚለው” ሲሉ የመንግሥታቸው አቋም ግልጽ አድርጓል። እዚህ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ብቻ ጠቀሱ እንጂ “ማህበረ ቅዱሳን” የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ሰላምን የሚፈታተን: የሃይማኖት ነጻነትን የሚጻረር: የዜጎች ሰብዓዊ መብትን የሚጋፋ አቋሙን የሚያንጸባርቅባቸው አባባሎችና ትምህርቶች በርካታ ናቸው።

* * * * *

“ማኅበረ ቅዱሳን” የሚያራግባቸው ቁንጽል መፈክሮች

በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘኑ፥

በእኛ በክርስቲያኖች ማለትም በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ከዘላለም ሞት መዳናችን የምናምን የእግዚአብሔር ልጆች በኩል ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ አንድና አንድ ነው ይኸውም፥ መፈክሩ እውን ክርስቲያናዊ መፈክር ነው ወይ? ነገሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘንስ ሚዛን ይደፋል ወይ? «አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት!» ብሎ የአዲስ ኪዳን እምነት ሆነ የክርስቶስ ኢየሱስ ትምህርት አለ ወይ? ነው። መልሱ አጭር ነው።

አንደኛ፡ በመጀመሪያ ደረጃ መጽሐፍ “በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” እንዲል ክርስትና በነቢያትና በሐዋርያት መሰረት ላይ የታነጸ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስለ ሰዎች በደል፣ ኃጢአትና መተላለፍ ተላልፎ የተሰጠ ብቸኛ አዳኝና ጌታ መሆኑን በማመን የሚገኝ የዘላለም ህይወት እንጅ ኢየሱስ ጓድ መንግሥቱ ኃይለማሪያም ሆኖ መፈክር እያሰማህ የምትከተለው አምላክ፤ ክርስትናም የፖለቲካ ድርጅት ፓርቲ አይደልም።

ሁለተኛ፡ በዮሐንስ ወንጌል 13: 35 “እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ” ተብሎ እንደተጻፈ ቀለል ባለ አማርኛ መፈክሩም ክርስቲያናዊ አይደለም አጋፋሪዎቹም ክርስቲያን/ የክርስቶስ ተከታዮች ሊሆኑ አይችሉም። አንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ የታጠበ፣ የተቀደሰና የጸደቀ ክርስቲያን በዕለት ዕለት ህይወቱ ተለይቶ የሚታወቀው በጸብ ጫሪነቱ፣ በተናዳፊነቱ፣ አልያም በነገር ሳይሆን የአንድ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ መለያው ፍቅር ነው። እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ በመንገዱ ሁሉ የሚያስበውና የሚያሰላስለው ፍቅር ነው። ቋንቋው ስራውም ሁሉ ፍቅርና የፍቅር ውጤቶች ናቸው። ፍቅር ካራሱ ጋራ፣ ፍቅር ከወገኖቹ ጋራ፣ ፍቅር ከጎረቤቱ፣ ፍቅር ከሚያምንም ከማያምንም ጋራ። ታድያ ይህ የክርስትናና የክርትያኖች መታወቂያ (ፍቅር ማለቴ ነው) ራሱ “የቅዱሳን ማህበር” በማለት የሚጠራ ግብረ እኩይ ማህበር በቅርብም በሩቅም በዞረበት: በዋለበት: ባለፈበትና ጥላው ባጠላበት ስፍራ ሁሉ እነዚህ ነገሮች የውሃ ሽታ ናቸው።

በነገራችን ላይ «አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት» የሚለውን አባባል “ሕገ መንግስት” ብቻ ሳይሆን ጸረ ክርስትና/ የክርስትናን መልክ ለማጥፋትና ክርስትናን የጥላሸት ለመቀባት በአዲስ ኪዳን ላይ የተቃጣ የጸረ- ክርስቶስ ሃሳዊ መሲህ አጀንዳ ነው። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ዓቢይ ነጥብ ቢኖር <u>እግዚአብሔር በግርግር፣ በአመጽ፣ በአድመኝነት፣ የማይከብር መሆኑና አመጸኝነት ለባህሪው የማይስማማው፤ ምግባረ እኩይ ልጅ የሌለው፤ ጻዲቅ አምላክ መሆኑ በግልጽ ሊታወቅና ሊሰመርበት ይገባል</u>።

ጌታችን ኢየሱስ በማቴ 28: 19 ለደቀመዛሙርቱ “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው” እንዲል ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ወደ ዓለም ስያሰማራ “እያስተማራችኋቸው” አለ እንጂ “ያልተጻፈ ቃል በቲሸርታችሁ ጽፋችሁ በታላቅ ጩኸትና ጭፈራ ዱላና ቆመጥም ይዛችሁ ተከታዮች አፍሩልኝ አላለም!” እንዲህ ያለ እንቅስቃሴም ከክርስቲያናዊ ስነ ምግባር የወጣ ተግባር ብቻ ሳይሆን ሰይጣናዊም ነው።

በፖለቲካ አነጋገር ኢትዮጵያ የሁሉም “ኢትዮጵያዊ ነኝ!” ብሎ የሚያምን ዜጋ ናት! ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ብቸኛ ጌትነትና አዳኝነት ቢያምንም ባያምንም፣ ቢቀበልም ባይቀበልም ኢትዮጵያ ለዚህ ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ ምድሩ፣ ኩራቱ፣ ሀገሩም ናት። በኢየሱስ ማመን ለራስ ጥቅም እንጅ ለእግዚአብሔር ተብሎ የሚደረግ ነገር አይደለም። ክርስትና፡ አላምንም

ያለ አንገቱን በሜንጫ ምታው/በስይፍ ቅላው የሚል ትምህርት የለውም። እንደው ግን በአባባሉ [«አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት» ማለት ነው] ያልተስማማ፣ በነጻ ፈቃ የሚያምን፣ የሌላ እምነት ተከታይ ዜጋ የት ይሂድ ነው መልእክቱ? በምድሪትዋ የተወለደ ሁሉ ምድሪቱ እኩል ትደርሰዋለች። "አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት" የሚለው ማኅበረ ቅዱሳናዊ መፈክር "ድምጻችን ያሰማ!" ከሚለው ኢስላማዊ (ጅሃዳዊ) ጩኸት ጋር ያስተያየነው እንደሆነ ሁለቱም የአንዲት ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

ወይ ጉድ! ክርስቲያን ለሰዎች የምስራች ቃል የሚናገርበት፣ ወንጌልን የሚመሰክርበት፣ የእውነትን ቃል በፍቅር የሚያካፍልበት መንገድ ለመፍጠር ይጠበባል እንጂ ያልደረሰበት/ያልነካውን ሰው በቡጢ ለማለት ለጸብ፣ ለነገር፣ ለደምና ለሞት አይተናኮስም አይነካካም። ለመሆኑ እንዲህ ያለ በክርስትና ስም ነገር ፍለጋ መሰማራት ከየት የተገኘ መገለጥ ነው?

አንዱ የሚያምነውን እምነት ሌላው ስላልተከተለ በአገሩ እንደ ባዕድ አቀርቅሮ የሚሄድበት ምንም ምክንያት የለውም። ይህን ሐቅ የማይቀበል ማንም ቢኖር ደግሞ ምድሪቱ እናት አገሩ መሆንዋ ትቀርና እስር ቤት ብትሆንበት ምን ይደንቃል? ይህ ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እምነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሀገራዊ ጥቅም ማእከል ያደረገ አጀንዳ ያላቸው ለህዝብ የቆምና ለሕዝብ የሚቆረቆሩ የፖለቲካ ድርጅቶች እምነት ሊሆን ይገባል።

በመቀጠል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉት ይህንኑ ነበር "እንደዚህ ዓይነት ነገር የሚናገሩና የሚያደርጉ ሰዎች ከግንዛቤ ችግር የተነሳ ሊሆን ስለሚችል በትምህርት ሊመለሱ እንደሚችሉ" ይላሉ። "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማ" ነው የሚባለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነገራቸው በፖለቲካ ቋንቋ ማስረዳታቸው ካልሆነ በስተቀር የ"ማህበረ ቅዱሳንና" ዓላማና ግብ (አጀንዳ) አንድና አንድ ነው። ይኸውም የሀገሪቱ ስልጣን በመላ ቤተ ክህነቱም ቤተ መንግሥቱም መቆጣጠር ነው። እንስቃሴው በተመለከተ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ነው የሚለው በበኩሌ እምነት ፍጹም ተቀባይነት የሌለውና ሊሆንም የማይችል ነው።

እዚህ ላይ ማህበሩ በቤተ-ክርስቲያን ጥላ ሥር ስለ ተጠለለ ብቻ ከቤተ-መንግስት አካባቢ መሰጠት የሚገባውን ስም አላገኘም። ቁምነገሩ "ማህበረ ቅዱሳን" ብዙዎች እንደሚያውቁት ነጭ ነጠላ ለብሶ ሲያሸበሽብ መላእክት የሚያስቀና መሆኑ ሳይሆን "ማህበረ ቅዱሳን" ማለት  በሽብር ድርጊት ላይ የተሰማራ ሀገርንና ትውልድን የማተረማመስ አጀንዳ ያለው ስራ ፈቶ የተደራጀ የአቡጊዳ ሸፍታ ስብስብ መሆኑ በሀገሪትዋ ጠቅላይ ሚኒስትር በማያዳግም ቋንቋ በይፋ መገለጹ ያስማማናል።  የማህበሩ ቋንቋ እንደ ገደል ማሚቱ የሚያስተጋባ ክፍል ብዙሐኑ የማህበሩ አባላት አንደሆነ ግን እውነትም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ በእጅጉ የሚያጥረው ዜጋ ለመሆኑ አያጠያይቅም።

ይህ ሁሉ ካስረዱ በኋም በሃይማኖት ሽፋን ሌላ ተልእኮ ስለሚያራምዱ እንደ "ማህበረ ቅዱሳን" ያሉ ለሀገርም ለወገን የማይበጁ ኪሳራዎች ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ መንግስታዊ አቋማቸውን ሲገልጹ የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ለዕብራውያን ሰዎች ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ (ዕብ. 12፡ 15) ገልጾ መቆረጥ እንደሚገባ ሲል በጻፈው መንፈስ ጠቅላይ ሚኒስትሩም "የሃይማኖት አክራሪነት በአጭሩ መቀጨት ይኖርበታል" በማለት ንግግራቸውን ቋጭተዋል።

በመጨረሻ ኃይማኖታዊ ጽንፈኝነት ምን ማለት እንደሆነና አስከፊ ገጽታውን በማሳየት ለምን መወገድ እንዳለበትም ጥቂት ነጥቦችን በመዘርዘር ልለያችሁ።

- ጽንፈኞች ከፉኛ በጅምላዊ አስተሳሰብ የተለከፉ ከመሆናቸው የተነሳ እንደ አማኝ እግዚአብሔር ምን ያላል? መጽሐፉስ? ማለት ቀርቶ ከእግዚአብሔርም ከቃሉም በላይ የሚከበሩና የሚፈሩ የድርጅቱ መሪዎች ስለሚሆኑ እገሌ ምን አለ? እየተባለ የጨለማ ቁራጭ የሲዖል ኢጋፋሪ ያለውን የአመጻ ቋንቋ እያስተጋባ ለጥፋት የሚሰለፍ ትውልድ ስለሚያፈራ።

- ጽንፈኞች ነፍሰ ገዳዮች ናቸው፥ “የአብርሃም ዘር መሆናችሁንስ አውቃለሁ ነገር ግን ቃሌ በእናንተ አይኖርምና ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ” እንዲል የዮሐንስ ወንጌል 8: 37, (ማቴ 23: 31)
- ጽንፈኞች ሐሰተኞ: ውሸተኞችም ናቸው፥ (2ኛ ቆሮ. 11: 13)
- ጽንፈኞች ተመጻዳቂዎች: ግብዞችም ናቸው፥
- ጽንፈኞች ከእውቀት ማነስ የተነሳ የሚፈጡሩ እውቀት አልባ ቀናኢያን ናቸው፥ (ማቴ. 22: 29)
- ጽንፈኞች ማንም ይሁን ምን የሚገባንን ያክል ከሚገባው ማህበረሰብ ጋር እንደ ሰው ሊኖር ስለሚገባ ሰብአዊ ግኑኝነት የሚያሻክሩ: ጸረ ሰብዓዊ ሙብት አቋም የሚያራምዱ: ለሕዝብ ሰላም ለሀገር ደህንነት ጠንቅ ናቸው፥
- ሃይማኖታዊ ጽንፈኝነት ጸረ- ዲሞክራሲዊ አስተሳሰብ የወለደው በየትኛውም መድረክ ተቀባይነት የሌለው ከይሳዊ አካሄድ ከመሆኑ በላይ የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ የሚገፋም ነው፥
- በአጠቃላይ "ማህበረ ቅዱሳን" ማለት ሌላ ማንም ሳይሆን ዘርዘር ባለመልኩ የተመለከትናቸውን መጠነኛ የጽንፈኞች መገለጫዎች የሚታዩበትና የሚንጸባረቁበት ሁነኛ አገር አጥፊ ማህበር ከመሆኑ በተጨማሪ በግርግር የሚያምን ድብቅ ፖለቲካዊ አጀንዳ ያለው መንፈሳዊ ካባ የተላበሰም ነው።

ስለሆነም በእኔ ላይ ብትፈርዱ ትበተናላችሁ: መንግስታችሁ አይጸናም እያለ በባዶ ሲያስፈራራና ሲያናፋ የነበረውን ለበርካታ ዓመታት ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ አኳኃን "ክንፍ አለው ይበራል አይሞትም ያርጋል" እየተባለ ሳይገባው ሲፈራና ሲከበር ብዙዎችን ለከፋ ችግር የዳረገ፣ የብዙዎችን ትዳር አናግቶ ቤተ-ሰብን ያፈራረሰ፣ ባለ አውልያና ባለ ክራማቱ "አባባ" ታምራት ያገኘች እጅ ታገኘው ዘንድ የዘወትር ጸሎቴ ነው።

ዲ/ን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል
Email: yetdgnayalehe@gmail.com
http://salsaywoyane.wordpress.com/
United States of America
Oct 14, 2012